# ለአባታችን ለብጹህ አቡነ ዜና ማርቆስ

(መታሰቢያ ከወንድወሰን ሰብሰቤ)




ምን ጉድ መጣብን ዘንድሮ አብይ ጾም፣

ወደመ ይሉናል የዘጌ ገዳም፣

ሊቃውንቱ ሁሉ እንግዲህ ያርምም፣

አመታት አስቆጠርን ታሪክ ሲወድም፣

እግዚዎ ማለት ያሻል ግቡልን ገዳም፣

ደብሎውን ዘንጉን ወዲአ ወርውራችሁ፣

ከተማ ለመኖር ድሎት የገባችሁ፣

ይህንን ስትሰሙ ምን አለ ውስጣችሁ፣

የተዋህዶ እምነት መሰረት ተናጋ፣

ዝም አለን አረፈ ዜና ማርቆስ ካልጋ፣

እንዲህ ሆኖ ቀረ የሊቅ ሁሉ ዋጋ፣

መቁዋሚያው ጽናጽል አልባሳት መስከሩ፣

ከበሮው መስቀሉ ዳዊትም ዘምሩ፣

እንግዲህ ተነስቱዋል እሩቅ ነው ሀገሩ፣

የተዋህዶ ልብስ ጌጡዋ ዜና ማርቆስ፣

ተዋህዶ አዝናለች እባክህ ተመለስ፣

በከሀዲ መንፈስ ቤቱዋ እንዲህ ሲታመስ፣

መቁዋሚያህን ይዘህ ከኛው ጋራ አልቅስ፣

አልችል አልኩኝ ዛሬ ባር ባር አለው ሆዴ፣

አዘኑ በዛብን ዘንድሮ ሁዳዴ፣

መቁዋሚያው ወድቆብን ልንሄድ ነው ዳዴ፣

ዝቁዋላ ቁልቢ ምን አሉ ሲሰሙ፣

አገልግሎ ነበር ባጥንቱ በደሙ፣

EthioLion.Com

ምን ይሉ እንግዲህ እውነትን ሲቀሙ፣
ዝቁዋላ አሰቦት ዋልድባም ነደዱ፣
አረ እግዚዎ በሉ በጊዜ ይወገዱ፣
ነደደ ይሉናል እነሱ ይንደዱ፣
የትዋህዶ ልጆች ሙሾውን አውርዱ፣
በአባቶቻችን ልብስ ቆመው ሲነግዱ፣
እነሱ ሲያብዱ ምንድን ነው መስገዱ፣
መከራው በረታ ተዋህዶ ደከመች፣
ወርቅ አልማዝ እንቁዋን እየተነጠቀች፣
አምላክ አዝኖብናል በተዋህዶ ልጆች፣
ነጎዱ ሂዱብን የተዋህዶ ሀብቶች፣
50 ዘመን ቤትሽ ቅኔ ተቀኝቶ፣
አሸብሽቦ አዚሞ ከበሮውን መቶ፣
ህያው ሊቀበር ነው ሰው ቀሞ ሞቶ፣
ጉምቱ ጉምቱ አባቶች በሞት ሲወሰዱ፣
ሀዘን እንቀመጥ ገዳማት ሲነዱ፣
ጉዳችን ጀመረ መቼ አበቃና፣
የተዋህዶ ልጆች በሉ ቀና ቀና፣
አልማዝ ወርቁ ሂዶ ሁዋላ እንዳንቀር ወና፣
እግዚኦ በሉ ቁሙ ተሰባሰቡና፣
ሁዋላ እንዳንቀር ወና፣

(Coventry, England)

EthioLion.Com